የሰ/መ/ቁ 105839

ሐምሌ 29/2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- ወ/ሮ የምስራች ሽፈራው ቀረቡ

ተጠሪ፡- አራዳ ክ/ከ/ወረዳ 6 ቀበሌ 11/12 ሽ/ን/የተ/የህ/ስራ ማህበር ጠበቃ ታሪኩ አስፋው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ሲሆን የአሁን አመልካች በፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት መናገሻ ምድብ 2ኛ የስራ ክርክር ችሎት በቀን 29/05/2006 ዓ.ም በቀረበ ክስ የተጀመረ ነው፡፡ በተከሳሽ ድርጅት የአሁን ተጠሪ ድርጅት ውስጥ ከህዳር 3/1977 ዓ.ም ጀምሮ በሂሳብ ሰራተኝነት የስራ መደብ በወር 1339 ብር እየተከፈላቸው ሲሰሩ እንደቆዩ በህመም ምክንያት ህክምና ላይ እንደነበሩ ከዚያ የአመት እረፍት ጠይቀው ስለተፈቀደላቸው ታህሳስ 5 ቀን 2006 ዓ.ም በፍቃዳቸው ስራውን የለቀቁ መሆኑ በመግለፅ ቁልፍና ካዝና እንዲረከባቸው የተለያዩ ክፍያዎች የስራ ልምዳቸው እንዲሰጣቸው እና የጡረታ የከፈሉትን ወደ ጡረታ ሚኒስተር እንዲዛፍላቸዉ ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በቀን 8/7/2006 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱ ደግሞ ሰለመታመማቸው የህክምና ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ በእጃቸው ያለው ንብረት ለእመቤት አስረክበው ፍቃዳቸው እንደወሰዱ በደብዳቤ ተገልፆላቸው ፍቃደኛ አልሆኑም ሳይጠቀሙ ቀርቷል፡፡ ሳያስረክቡ በገዛ ፍቃዳቸው ስራ አቁመዋል፡፡ ለንብረቱ ሀጋዊ ነው የስራ ስንብት አይከፈላቸውም ምክንያቱም የጡረታ ተጠቃሚ ስለሆኑ፡፡ በገዛ ፍቃዳቸው የለቀቁ ስለሆነ መብት የላቸውም፡፡ የምንከፍለው ክፍያ የለም ንብረት ሳያስረክቡ ለዘገየበት አይጠየቁም እረፍት አመት መዛወሩን አናውቅም ከ2 አመት ሊረዝም አይችልም፡፡ 64 ሰዓት ትርፍ መስራታቸው ማስረጃ አላቀረቡም በደመወዝ መክፈያ ቀን የሚጠየቅ ስለሆነ በይርጋ ቀሪ ነው የጡረታ የከፈሉት በየወሩ የሚተላለፍላቸው ነው፣ ክሊራንስ ካቀረቡ ምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል፣ ማስጠንቀቂያ ስይሰጡ ስራቸውን ስላቋረጡ ካሳ ሊከፍሉን ይገባል በማለት መልስ ሰጥቶ ተከራክሮአል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ከሳሽ የስራ ውላቸውን ለማቋረጥ የተገደዱት ተከሳሹ በተደጋጋሚ የአመት ፈቃድ ሊሰጣቸው ፈቃደኛ ሳይሆን በመቅረቱ እንደሆነ በመረጋገጡ ከሳሽ በራሳቸው አነሳሽነት የስራ

ውላቸውን በማቋረጥ የወሰዱት እርምጃ ሕጋዊ መሆኑን፣ ከሳሽ ከአምስት ዓመት በላይ ያገለገሉ ቢሆንም የጡረታ ተጠቃሚ በመሆናቸው የሰራ ስንብት ክፍያ ሊከፈላቸው የሚችልበት አግባብ አለመኖሩን፣ ከሳሽ በዕረፍት ቀናት ማለትም ቅዳሜ እና እሁድ የሰሩበት እንዲከፈላቸው የጠየቁ ቢሆንም በእነዚህ ቀናት እንደሰሩ ግልፅ ትዕዛዝ የተሰጣቸው ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ ባለመኖሩ ሊከፈላቸው የማይገባ መሆኑን፣ ይሁን እንጂ ከሳሽ ሰርተው ያልተከፈላቸው የአምስት ቀናት ደመወዝ ብር 223.20 የ79 ቀትና የአመት ዕረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ ብር 3,526.00 እና ክፍያ የዘገየበት የሶስት ወር ደመወዝ ብር 4017.00 በድምሩ ብር 7766.20 /ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ስልሳ ስድስት ከሃያ ሳንቲም/ ሊከፈላቸው ስለሚገባ ተከሳሹ ይህንኑ ገንዘብ ከወጪ ኪሳራ ብር 400 /አራት መቶ/ ጋር ለከሳሽ እንዲከፍል እና የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ይግባኝ ሰሚው ከ/ፍ/ቤት የቀረቡለትን ይግባኝ ዘግቶ በማሰናበቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ የአመልካች የአገልግሎት ዘመን 29 አመት መሆኑ ባልተካደበት የግል ድርጅቶች ሰራተኞች የጡረታ መብት እንዲያገኙ የተደረገው በደንብ ቁጥር 46/2004 በመሆኑ አመልካች የአሁን ጡረታ የሚከፈላቸው መሆኑ ባልተረጋገጠበት የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄአቸው ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ተጠራው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርመረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች ስራቸውን በፈቃዳቸው የለቀቁት 29 አመታት ካገለገሉ በኋላ ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ አመልካች 29 አመት ያገለገሉ ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ የለም በማለቱ ተጠሪው በሰጠው መልስ ያቀረበው ክርክር በስር ፍ/ቤቶች ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ውጪ የቀረበ እና አዲስ ክርክር በመሆኑ ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባው አይደለም፡፡ ቢያነስ አምስት አመት በአሰሪው ዘንድ የሰራ አገልግሎት ኖሮት ስራው ላይ የማያስቆይ ከስልጠና ጋር የተያያዘ ለአሰሪው የውል ግዴታ ሳይኖርበት ሰራውን በገዛ ፈቃዱ የለቀቀ ሰራተኛ የሰራ ስንብት የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 /በአዋጅ ቁጥር 494/98 እንደተሻሻለ/ በአንቀፅ 39/1/ሸ/ ስር በግልፅ ተመልክቷል፡፡ አመልካች የጡረታ መብት ያላቸው መሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም የጡረታ አበልን አሁን መቀበል እንዳልጀመሩ እና መብቱ ተፈፃሚነት የሚኖረው በጡረታ ዕድሜ ላይ ሊከፈሉ መሆኑ አላከራከረም፡፡

ከአምስት አመት በላይ አገልግሎት ኖሮት ስራውን በገዛ ፈቃዱ የለቀቀ ሰራተኛ የጡረታ መብት ተጠቃሚ ቢሆንም የጡረታ አበሉን ማግኘት የሚጀምረው ስራውን እንደለቀቀ ወዲያውኑ መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መበት ያለው ስለመሆኑ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አገልግሎት ያላቸው የአዋጁን ድንጋጌዎች በመተርጎም በመ/ቁ 39808 በ21/11/2001 ዓ.ም እና በሌላቸው መዛግብት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ ይህ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ለተያዘው ክርክር ተፈፃሚነት ያለው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪው በመልሱ ላይ የገለፀው በሰበር መዝገብ ቁጥር 35197 የተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ስራውን በራሱ ፈቃድ ለቆ የኘሮቪደንት ፈንድ የተከፈለው ሰራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ በተደራቢነት የማግኘት መብት እንደማይኖረው የተወሰነበት በመሆኑ በዚህ መዝገብ ከተያዘው ክርክር ጋር ግንኙት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት እና ሊታረም የሚገባው በመሆኑ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፊ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 44757 በ29/09/06 ተሰጥቶ በፊ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 155657 በ22/11/06 በትዕዛዝ በፀናው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የአምስት ቀናት ደመወዝና የ79 ቀናት የአመት አረፍት ክፍያ እና ክፍያ የዘገየበት በድምሩ ብር 7766.20 /ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ስድሳ ስድስት ከ20/100/ ተጠሪው ለአመልካች እንዲከፈል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. የአመልካችን የሰራ ስንብት ክፍያ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
4. የስራ ስንብት ክፍያ በአመልካች የአገልግሎት ዘመን እና የደመወዝ መጠን ተሰጥቶ የሚገኘውን ውጤት ብር 13,836.33 /አስራ ሶስት ሺህ ስምንት መቶ ሰላሳ ስድስት ከ33/100/ ተጠሪው ለአመልካች እንዲከፍል ወስነናል፡፡
5. የውሳኔው ግልባጭ በውሳኔው መሰረት እንዲያስፈፅም ለፊ/መ/ደ/ፍ/ቤት እንዲያውቀው ዳግም ለፊ/ጠ/ፍ/ቤት ይላክ፡፡
6. በስር ፍ/ቤት የተወሰነው በወጪና ኪሳራ ውሳኔ እንደተጠበቀ ሆኖ የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ